# እድገት እና የአስተዳደግ ልክ አመልካቾች

ሕጻናት ጤናማ ሆነው ለማደግ ከምግብና ከውሃ በላይ ያለፈ በርካታ ነገሮች ያስፈልጓቸዋል። ከነዚህ ተጨማሪ ነገሮች መካከልም፣ ፍቅር፣ ግንዛቤ፣ አመራር፣ ክብካቤና እና ጥበቃ ያስፈልጋቸዋል። ስለራሳቸው ዓለም ለመማር፣ ሙያንና ጥበብን ለማዳበር፣ እንደዚሁም ዘውትር ተለዋዋጭ ከሆነው ፍላጎታቸው ጋር እራሳቸውን ለማጣጣም ይችሉ ዘንድ የርስዎን እርዳታ ይፈልጋሉ።

በልጅዎ የአስተዳደግ ሂደት ላይ ፈጣን፣ ርቱዕና አመርቂ ሚናን መጫወት በጣም የሚያስደስት፣ የሚያበለጽግ፣ እና መጨረሻውም በጣም የሚያረካ እና የልፋተዎን ዋጋ የሚከፍል ሊሆን ይችላል። በአመዛኙ፣ በየዕለቱ በልጅዎ ላይ የተለያዩ ለውጦችን፣ ለምሳሌ የአካል፣ የባህሪ፣ እንድሁም የቋንቋ ለውጦችን ያስተውላሉ። ከዚያም የልጅዎ ጥሩ አስተዳደግ፣ በሂደቱ እርሰዎ በሚያደርጉት ጥሩ ተሳትፎ ላይ የተመሰረተ እንደሚሆን ወዲያውኑ ይገነዘባሉ።

የልጅዎን እድገት ሲመለከቱና ሲገመግሙ፣ ሁለት የተለያዩ ሕጻናት በፍጹም አንድ ዓይነት ሊሆኑ እንደማይችሉ በአዕምሮዎ ግንዛቤ ይያዙ። አንዳንድ "ዓይነተኛና የተለመዱ" የእድገት ደረጃዎች ሲኖሩ፣ ምናልባትም የርስዎ ልጅ የአስተዳደግ ርምጃ ከሌላው ልጅ የተለየ ሊሆን ይችላል። በተጨማሪም፣ ልጅዎ በአንድ የተወሰነ ሁኔታ ላይ በጣም በፍጥነት ሊያድግ ሲችል፣ በሌለኛው ሁኔታ ላይ ግን ይህ ላይሆን ይችላል።

ልጅዎ በአንድ የተወሰነ ዕድገታዊ ሁኔታ ላይ ችግር እየገጠመው/እየገጠማት እንደሆነ ካመኑ፣ "አይደደናገጡ"። ከእድገታዊ ሁኔታ ጋር የተለያያዙ በርካታ ፈታኝ ሁኔታዎች፣ በቅድመ-እገዛ ጣልቃ ገብነት - *ማለትም አንድ ልጅ ዕድሜው/ዕድሜዋ ለትምህርት ከመድረሱ/ከመድረሷ በፊት የልጁን/የልጅቷን የማደግ/የመዳበር እምቅ ኃይል ለማነቃቃትና ለማዳበር በሚሰጡ* አገልግሎቶች አማካኝነት ሊታገዙ ይችላሉና።

በዚህ ብሮቸር ውስጥ የተካተቱት መረጃዎች ሁሉንም ዓይነት የሚያጠቃልሉ እንዲሆኑ ታቅደው የተዘጋጁ አይደሉም። ሆኖም ግን ልጅዎ በተወሰነ የዕድሜ ደረጃ ላይ ሳለ/ሳለች ምን ምን ሊያደርግ/ልታደርግ እንደሚችል/እንደምትችል አጠቃላይ መመሪያን በማቅረብ በጣም ጠቃሚ ሊሆን ይችላል።

ይህን መረጃ በቀላሉ ብድግ አድርገው ሊመለከቱት በሚችሉበት፣ በደንብ በተጠበቀና በቀላሉ ማግኘት በሚቻልብዎት ቦታ ያስቀምጡት—ምናልባትም በፋይል ማቀፊያ፣ ወይም በፎቶግራፍ አልበም፣ በሕጻናት መጽሐፍ ውስጥ፣ ወይም የቤተሰቡን ሰንድ ነክ ጉዳዮች በሚያስቀምጡበት ቦታ ሊያስቀምጡት ይችላሉ። ጥያቄ ካለዎት፣ ለአካባቢዎ የሕጻናንትና ድክ-ድክ ባይ ልጆች መርሃ-ግብር ይደውሉ።

## ልደት—2 ወራት

*አካላዊ እድገት*

- እራሱን ከመሬት በላይ በጣም በጥቂቱ ቀና ያደርጋል
- እጁን ጥብቅ አድርጎ ቡጢውን እንደጨበጠ ይቆያል

*የንግግር እድገት*

- ጉጉ ይላል፣ እንደዚሁም የሚውተመተም ድምጽ ያወጣል
- ይኮላተፋል

*ማህበራዊ እድገት*

- ብዙ ይተኛል
- ብዙ ያለቅሳል
- ያልተስተካከለ የመኝታና የአመጋገብ ሁኔታ ሊታይበት ይችላል
- የወላጆችን ፊት ሲያይ እና ድምጻቸውንም ሲሰማ ጸጥ ይላል

## 2 ወራት

*አካላዊ እድገት*

- በሆዱ እንደተጋደመ እራሱን ቀና ያደርጋል
- ብዙ እንቅስቃሴዎች ያደርጋል
- ቡጢውን ያላላል፣ የታጠፉ ጣቶችን ይዘረጋል
- በጀርባው እንደተንጋለለ እጁን ያውለበልባል፣ እናም እግሮቹን ያወናጪፋል

*የንግግር እድገት*

- ጉጉ ይላል፣ በተለይም ሰው ሲያወራው ደግሞ፣ በመንዶቅዶቅ ዓይነት ይስቃል፣ ይፈነድቃል
- ለተለያዩ ዓይነት ፍላጎቶቹ የተለያዩ ዓይነት ለቅሶዎችን ያለቅሳል

*ማህበራዊ እድገት*

- ፈገግታን ማሳየት ይጀምራል፣ መደሰትንና መከፋትን ያሳያል
- የተለመዱ ድምጾችን ሲሰማ ዞር ይላል
- ሲታቀፉት ጸጥ ይላል
- ሲኮረኮር ደስ ይለዋል
- መጋቢው ሲመግበው ለአጪር ጊዜ ብቻ ዓይን-ለዓይን ይገናኛል
- ራሱን ጸጥ ለማሰኘት አውራ ጣቱን ወይም የእጅ ጣቶቹን ሊጠባ ይችላል

## 4 ወራት

*አካላዊ እድገት*

- ክፍሉን በሙሉ መቃኘት/መመልከት ይችላል
- ሲደገፍ ቀጥ ብሎ ይቀመጣል
- በሆዱ ተኝቶ ከነበረብት ሁኔታ በጀርባው ይገለበጣል
- የመጫዎቻ አሻንጊሊቶቹ ጋ ይደርሳል
- ቁሳዊ እቃዎችን በእጁ ይይዛል
- የእግሮቹን ጣቶች በመያዝ እስከ አፉ ድረስ ያመጣቸዋል
- የተለመዱ ድምጾችን ሲሰማ ራሱን ዞር ያደርጋል
- ሰዎችን በዓይኑ ይከተላል

*የንግግር እድገት*

- ይስቃል፣ ይጮሃል፣ ይንተባተባል/ይኮላተፋል
- በደስታ ያጉረመርማል፣ ይንዶቀዶቃል
- "ኡውው" እና "ኣሃሃ" ይላል

*ማህበራዊ እድገት*

- ከራሱ እግር ጋ መጫዎትን ይወዳል
- ከጥቁርና ነጭ ይልቅ ቀለማትን ያያል
- ብድግ ተደርጎ እንዲታቀፍ ሲፈልግ ይጨቃጨቃል
- በቤተሰቡ አባላት መካከል ያለውን ልዩነት መናገር ይችላል
- ለመጫዎት እጆቹንና ክንዶቹን እውጥቶ ይዘረጋል
- ፈገግ ይላል

## 7 ወራት

*አካላዊ እድገት*

- ለአጪር ጊዜ ራሱን ችሎ ቁጭ ሊል ይችላል
- መጫዎቻ አሻንጉሎቶችን በእጁ ይይዛል፣ ጥቃቅን ምግቦችንም እያነሳ ሊበላ ይችላል
- ደገፍ ተደርጎ ሲያዝ ይቆማል፣ የተወሰነ ክብደቱንም በራሱ እግሮች ላይ ሊያሳርፍ ይችላል
- ቁሳቁሶችን ብድግ ያደርጋል፣ ከአንደኛው እጁ ወደ ሌላኛው እጁም ያስተላልፋቸዋል
- ምናልባት የመኝታ ሁኔትውን የሚረብሸው ቢሆንም የወተት ጥርስ ማውጣት ይጀምራል

*የንግግር እድገት*

- አናባቢ ድምጾችን ያቀላቅላል
- ድምጾችን ይኮርጃል
- "እምቢ" የሚለው ቃልና የራሱ ስም ሲጠራ ምላሽ ይሰጣል
- መግባባትን ለመጀመር አካላዊ ቋንቋን ይጠቀማል

*ማህበራዊ እድገት*

- ብቻውን ይጫዎታል
- ከሰዎችና ከመጫዎቻ አሻንጉሊቶች ጋር ረዘም ላለ ጊዜ ይጫዎታል
- ሌሎች ልጆችን ማየት ይወዳል
- ለድምጽ የሚኖረው ምላሽ የበለጠ ይዳብራል
- እንግዶችን ይርቃል፣ ከሚያውቃቸው አሳዳጊዎቹ ጋር ይጣበቃል

## 10 ወራት

*አካላዊ እድገት*

- የተለያዩ ያዳዳኸ ስልቶችን እየተጠቀመ ይድኻል
- በቁሳቁሶች ላይ ሁሉ ይድኻል
- አንድን ቁሳዊ እቃ ተደግፎ መቆም ሊጀምር ይችላል
- በእጁ ጣቶችና በአውራ ጣቱ በመጠቀም ትንንሽ ነገሮችን ያነሳል

*የንግግር እድገት*

- "እምቢ"፣ "ቻው" "ባባ" "ማማ" ይላል
- እድማጭ ለማግኘት ድምጹን ይጠቀማል

*ማህበራዊ እድገት*

- የበለጠ በራሱ ይተማመናል/ራሱን ይችላል ÷ ከመታቀፍ ይልቅ ብቻውን ቢጫዎት ይወዳል
- የፊትና የእጅ እንቅስቃሴዎችን ይኮርጃል
- ወላጆቹን ለመፈለግ በአካባቢው ላይ ይድኻል
- ስሙን ሲጠሩት ወደርሰዎ እየዳኸ ይመጣል
- "ሸሸጎት" መጫዎት ይወዳል
- ጭብጥ የሚሞሉ የመጽሃፍትና የመጽሄት ገጾችን ይገለብጣል
- የድምጽ ጨዋታ መጫዎት ይወዳል
- "ቻው" ለማለት እጁን ያውለበልባል
- ቀላል ትዕዛዛትን/መመሪያዎችን ይገነዘባል

## 12 ወራት

*አካላዊ እድገት*

- ከመዳኸ ለመውጣት እግሮቹን በሰፊው ከፈት አድርጎ በመንገዳገድ የመራመድ ሙከራ ይጀምራል
- በእጅ የሚበሉ ምግቦችን ይበላል
- ማንኪያ መጠቀም ሊጀምር ይችላል
- ቁጢጥ ይላል

*የንግግር እድገት*

- የሚፈልጋቸውን ሰዎች ለማመልከት "ባባ" እና "ማማ" የሚሉትን ቃላት ይጠቀማል
- ከ3 እስከ 10 የሚደርሱ "ትክክለኛ" ቃሎችን ይይዛል
- በአካላዊ ቋንቋው ላይ እንቅስቃሴ ይጨምርበታል

*ማህበራዊ እድገት*

- አድማጭ ይፈልጋል
- በከለር ይሞነጫጭራል
- ብዙ የተለያዩ የጨዋታ ዓይነቶች ይኖሩታል
- ከፍተኛ የመውደድና የመጥላት ሁኔታዎችን ያሳያል
- ከራሱ ጋር ይጫዎታል እራሱንም በመስታዎት ውስጥ ይስማል
- በአሻንጉሊቶችና በእንስሳት ምስሎች ይጫዎታል
- በመጽሃፍ ውስጥ ያሉ ስዕሎችን ያመለክታል፣ ምንነታቸውንም ይለያል
- ለምሳሌ "ወደ አባባህ ና።" የሚሉትን ቀላል ቃላት ይረዳል

## 15 ወራት

*አካላዊ እድገት*

- ብቻውን ይቆማል፣ ይራመዳል
- ራሱን ለመመገብ ማንኪያ ይጠቀማል
- ከሚራመድባቸው ቦታዎች አካባቢ እቃዎችን ያነሳል

*የንግግር እድገት*

- ቀላል ቃሎችንና ሃረጎችን ይጠቀማል
- በወላጆች የሚነገሩ አንዳንድ ቃሎችን ይናገራል

*ማህበራዊ እድገት*
- ሙዚቃ ማዳመጥና በዜማው መደነስ ይወዳል
- "እምቢ" ይላል ከዚያም ምግብ አልበላም ይላል
- አካባቢውን በሚገባ ይረዳል
- ይበልጥ እራሱን ወደሚችልበት ደረጃ እይደገ ነው
- በጣም ቅብጥብጥና ፈጣን ነው

## 18 ወራት

*አካላዊ እድገት*
- እየተግተረተረ ይሮጣል
- ኳስ ሲጫዎት ሙሉ እጁን ይጠቀማል
- እራሱን ችሎ ይበላል፤ በማንኪያ ይበላል፤ በሹካም ይሞክራል
- ጫማዎቹን፤ ኮፍያውን፤ ጓንቱን ያወልቃል
- ሣብ-ሣብ ማድረግ፤ ግትር ብሎ መጎተት፤ መደፋፋት፤ መግፋት፤ እና መሳብ ይወዳል
- ካለምንም እርዳታ ደረጃዎችን ወጥቶ ይወርዳል

*የንግግር እድገት*
- የዕቃዎችን ስም ያውቃል
- ሰውኛ ተውላጠ-ስሞችን ይጠቀማል

*ማህበራዊ እድገት*
- ፈልጎ ማግኘትን ያፈቅራል
- አዘውትሮ ምግብ እምቢ ይላል

## 24 ወራት

*አካላዊ እድገት*
- እራሱ ልብሱን ያወልቃል (ለምሳሌ እንደ ቢጃማ ያሉ ትልልቅ ልብሶችን)
- መራገጥ ይጀምራል
- ኩባያውን በደንብ አድርጎ ይይዛል
- ነገሮችን ይበታትንና እንደገና ደግሞ እንደነበሩ አድርጎ ይገጣጥማቸዋል

*የንግግር እድገት*
- የበለጠ ግልጽ አድርጎ ይናገራል
- "የሕጻን" ቋንቋን በአጫጭር ዓረፍተ-ነገሮች ይተካቸዋል
- ለራሱ ማውራት ይወዳል
- ሌሎች የሚናገሯቸውን ቃላት ይደግማቸዋል
- ቃላትን ከድርጊትን ጋር ያዛምዳል

*ማህበራዊ እድገት*
- አካባቢውን ይለያል
- እናቱንና አባቱን መርዳት ደስ ያሰኘዋል
- ከጨዋታ በኋላ እቃዎቹን መሰብሰብና አካባቢውን ንጹህ ማድረግ ሊያስደስተው ይችላል
- በጣም ፈጣን ነው
- ጊዚያዊ የንዴት ጠባይ ሊኖረው ይችላል
- ስማቸው ሲጠራለት የሰውነት ክፍሎችን ሊያመለክት ይችላል

## 36 ወራት

*አካላዊ እድገት*
- ዥዋዥዌ ይላል፤ የሆነ ነገር ላይ ይንጠላጠላል
- ከሆነ ቦታ ላይ ይዘላል
- ወደኋላ ይራመዳል
- ባለ-ሦሥት-ጎማ ብስክሌት ይጋልባል

*የንግግር እድገት*
- አጫጭር ዓረፍተ-ነገሮችን ተጠቅሞ ይናገራል፤ ከቃልትም ብዙ ቁጥሮችን ይጠቀማል
- አጫጭር መዝሙሮችን ይዘምራል
- የሚናገረው ቋንቋም ከወላጆቹ ውጪ በሆኑ ሰዎች ዘንድም ግንዝቤን ያገኛል
- የራሱን ስም ይናገራል
- "እምቢ" የሚለውን ቃል በጣም በብዛት ይጠቀማል
- ፍርሃትና ጥላቻውን ይገልጻል

*ማህበራዊ እድገት*
- በማንኪያና ሹካ በደንብ አድርጎ ይበላል
- በመምጠጫ ይጠጣል
- ትልልቅ ዶቃዎችን በክር ላይ ይሰካል
- እራሱ በራሱ በደንብ እድርጎ ልብሱን ይለብሳል
- የጾታ ሚናን መለየት ይጀምራል
- ከቤት ውጪ ያለውን አካባቢ በሚገባ ይቃኛል

## ለወላጆች የሚሆኑ አጫጭር ምክሮች

- ሌሎች ሲነጋገሩ ሲሰሙ፤ ሕጻናት መናገር ይማራሉ። ለልጅዎ ያውሩለት፤ ይዘምሩለት፤ ያንብቡለት።

- ሕጻናት አካላዊ ንክኪን ይወዳሉ። ልጅዎን ይንኩት፤ ያዝ-ለቀቅ ያድርጉት።

- ሕጻናት ጭንቀት ይሰማቸዋል። ልጅዎ ሲያለቅስ ፈጥነው በመድረስ በፍቅር እፍ እድርገው ያረጋጉት። ሌሎች ሰዎች ባሉበት ሁኔታ ለልጅዎም ሆነ ለሌሎቹ ሲያወሩ ጥንቃቄ ያድርጉ።

- የሕጻናት ፍላጎት ወደውጪው አካባቢያዊ ዓለም እንዲያዘነብል ተፈጥሮ ትገፋፋቸዋለች። ልጅዎን ይዘው ከቤት ውጪ አዘውተረው ይንቀሳቀሱ። አዲሱ አየርም እንደዚሁ ጥቅም አለው።

- ከልጅዎ እድሜና የእድገት ሁኔታ ጋር የሚስማሙ አሻንጉሊቶችን ለልጅዎ ያቅርቡለት። ተንቀሳቃሾች፤ በቀለማት ያሸበረቁ ሳጥኖች፤ ሳብ/ጎትት እሻንጉሊቶች፤ ትልልቅ ብሎኮች፤ ትልልቅ ኳሶች፤ እናም የሙዚቃ መሳሪያዎች ሁሉም ጥሩ ሃሳቦች ናቸው።

- ልጅዎን በጥንቃቄ ይያዙ። ሕጻናትና ከፍ-ከፍ ያሉሉ ልጆች ፈጽሞ መነቅነቅ/መወዝወዝ የለባቸውም!


የሜሪላንድ ግዛት የትምህርት ክፍል
የልዩ ትምህርት ዘርፍ/
የቅድመ-እገዛ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶች
ሜሪላንድ የጨቅላ ሕጻናትና ድክ-ድክ ባዮች መርሃ-ግብር
200 West Baltimore Street, 9th Floor
Baltimore, MD 21201
ስልክ፡ 410-767-0261
የነጻ ጥሪ፡ 1-800-535-0182
ፋክስ፡ 410-333-2661
የደንቆሮዎች የቴሌ መገናኛ መሳሪያ (TDD): 410-333-0731



Robert L. Ehrlich, Jr.
*ገዢ*

የሜሪላንድ ግዛት የትምህርት ቦርድ
Edward L. Root, *ፕሬዚደንት*
Jo Ann T. Bell, *ምክትል ፕሬዚደንት*
Philip S. Benzil
Dunbar Brooks
Calvin D. Disney
Clarence A. Hawkins
Walter S. Levin
Karabelle Pizzigati
Maria C. Torres-Queral
John L. Wisthoff
Christopher J. Caniglia

Nancy S. Grasmick
*የግዛታዊ ትምህርት ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ*

Carol Ann Baglin
*ተባባሪ የግዛታዊ ትምህርት ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ፤ የልዩ ትምህርት ዘርፍ/የቅድመ-እርዳታ ጣልቃ-ገብነት አገልግሎቶች*



የሜሪላድ ግዛት የትምህርት ክፍል፤ በቅጥር ሁኔታ ላይ ወይም ደግሞ አንዳንድ የመርሀ-ግብር ተሳትፎዎችን በሚመለከት ተጽዕኖ ሊያደርግ የሚችል፤ በጎሳ፤ በቀለም፤ በጾታ፤ በዕድሜ፤ በብሄር፤ በሀይማኖት፤ ወይም በአካለ-ጎደሎነት ላይ የተመሰረተ ምንም ዓይነት ልዩነትን አያደርግም። የትምህርት ክፍሉን ፖሊሲዎች ለሚመለከቱ ማንኛቸውም ዓይነት ጥያቀዎች፤ ለእኩልነት ማረጋገጫ ዋስትና እና የአቤቱታ ቅርንጫፍ በስልክ፤ 410-767-0246, ፋክስ፤ 410-333-8165 ወይም በደንቆሮዎች የቴሌ መገናኛ መሳሪያ አማካኝነት (TDD) 410-333-6442 ያነጋግሩ። ♦ ይህ ሰነድ ከዩ.ኤስ የትምህርት ክፍል፤ ከልዩ ትምህርትና የመቋቋሚያ አገልግሎቶች ቢሮ በተገኘ ገንዘብ፤ በልዩ ትምህርት ዘርፍ/የቅድመ-እገዛ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶች፤ IDEA ክፍል C፤ ችሮታ #H181A020124 መሰረት ዳብሮና ታትሞ የተዘጋጀ ነው። በዚህ ሰነድ ውስጥ የተገለጹት አመለካከቶች የግድ የዩ.ኤስ የትምህርት ክፍልንም ሆነ ወይም የማንንም ሌላ የፌዴራል ኤጀንሲን አመለካከት የሚያንጸባርቁ ላይሆኑ ይችላሉ፤ በዚህ መልኩም መወሰድ የለባቸውም። መረጃው ክህትመት ህግ (ኮፒ ራይት) ነጻ ነው። አንባቢዎች ቅጂውን እያባዙ በመጋራት እንዲያነቡት ይበረታታሉ፤ ሆኖም ግን፤ በሜሪላንድ ግዛት የትምህርት ክፍል፤ ለልዩ ትምህርት ዘርፍ/የቅድመ-እርዳታ-ጣልቃገብነት አገልግሎቶች መሰጠት ያለበትን ዋጋ አይዘንጉ። ♦ በአሜሪካዊያን አካለ ጎደሎዎች ድንጋጌ (ADA) መሰረት፤ ይህ ሰነድ በተጠየቀ ጊዜ በተለያዩ አማራጭ የአቀራረብ ስልቶች ዝግጁ ሆኖ ይገኛል። የልዩ ትምህርት ዘርፍ/ቅድመ-እገዛ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶች፤ የሜሪላንድ ግዛት የትምህርት ክፍልን በስክ፤ 410-767-0249 ፋክስ፤ 410-333-8165 የደንቆሮዎች የቴሌ መገናኛ መሳሪያ (TDD) 410-333-0731 አማካኝነት ያነጋግሩ።



4/04


# እድገት እና የአስተዳደግ ልክ አመልካቾች



## ከልደት እስከ ሦሥት ዓመት የእድሜ ክልል ውስጥ ስለሚገኙ ወጣት ሕጻናት የአስተዳደግ መመሪያ

የሜሪላንድ ግዛት የትምህርት ክፍል